ጠበኛ እውነቶች
በሜሪ ፈለቀ
ገፅ ብዛት=252
2012ዓ.ም




ይህ መፅሐፍ በ4ክፍሎች የተከፈለ ልብወለድ ሲሆን የተለያዩ ማህበራዊ እና ግላዊ ሕይወትን የሚዳስስ መፅሐፍ ነው።በአራቱም ታሪኮች መግቢያ ገጽ ላይ እነዚህ ከታች ያሰፈርኳቸው የታሪኩን አንጓ የሚያሳዩ ጥቅሶች ተቀምጠዋል ።

🚢**1.ቅዳሴና ቀረርቶ**

<<. እውነታው ሰዎች ሊያወድሱህ ከፈለጉ ከፈጣሪ ታናሽ ያደርጉሃል። ሊዘልፉህ ከፈለጉ ደግሞ ሳጥናኤል የሚቀናበት ክፍ ያደርጉህል። ከሰማሃቸው ደግሞ ራስህን የመሆን እድል አይሰጡህም። ሁሉም በፈለጉት መንገድ ሊቀርፁህ መጥረቢያ ይስላሉ። ልብህን ከከፈትክላቸው የየድርሻቸውን ጠርበውህ ቅርፅ አልባ ያደርጉሃል።>>

**2.ቀላውጥ ማስመለስ**

<<ሲገባኝ ሁሉም ሰው የሆነች<<የለውጥ ኩርባ>>አላቸው። አስተሳሰቡ ወደ ስሜቱ ወደ ድርጊቱ የሚቀየርበት።ወደ አዲስ ምዕራፍ የሚታጠፍበት ወይም ከወደቀበት መቀመቅ የሚስፈነጠርበት ወይም ለዛለው ጉልበቱ የሚያገኝበት። >>

3.እናቴን ተመኘኋት

<<በተለያየ መኻታ በተለያዩ እንቅልፍ ውስጥ አንድ አይነት ህልም እንዴት ይታለማል?የሆነ ሰው ያለፈበት መንገድ እና የደረሰበት ስኬት እንዴት የሌሎች ብዙዎች መንገድና መድረሻ ይሆናል?የሌሎች ብዙዎች ደስታ በአንድ ሰው መድረሻ እንዴት ይፈጠራል?>>

4.ምርጫ አልባ ምርጫ

<<ሁሌም ዛሬ ላይ ቆመህ ሁለት ምርጫ አለህ። ትናንት ወይም ነገ፤ትዝታ ወይም ተስፍ!>>

በመጨረሻም እንዲህ ትለናለች

<<ብሩህ ነገ የሚባል ቀን የለም።ማንም ቢሆን ነገን ኖሮ የሚያውቅ የለም።ምክንያቱም ነገን ለመኖር ስንጀምር ዛሬ ተብሏል።ብዙዎቻችን ግን ሁሌም ብሩህ ነገን ለመኖር ስንናፍቅ ብዙ ዛሬያችን ያልፈናል። እኛም ብሩህ የሚባል ቀን ሳይኖረን እናልፍለን። ብሩህ ቀን በእጃችን ያለው ዛሬ ነው። >>